የሰበር መ.ቁ. 27574

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ

ተጠሪ፡- የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአፈፃፀም የተያዘን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ ባለመብት፤ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በሰኔ 26 ቀን 1996 ዓ.ም በሽምግልና ጉባዔ ተሰጠ የተባለው ነው፡፡ የፍርድ ባለአዳው ለአፈፃፀም ክሱ በሰጠው መልስ ለአፈፃፀም የቀረበው ውሣኔ በአስታራቂ ሽማግሌዎች የተሰጠ የድርድር ሃሣብ እንጂ በፍ/ቤት የሚፈፀም ውሣኔ አይደለም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይህን ክርክር በመቀበል ለአፈፃፀም የቀረበው ውሣኔ ስልጣን ባልተሰጣቸው አስታራቂ ሽማግሌዎች የተሰጠ ነው፡፡ በግልግል ዳኞች እንደተሰጠ ተቆጥሮ የሚፈፀም አይደለም በማለት የአፈፃፀም ክሱን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጎአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 17 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪውን አስቀርበን ክርክሩን



አሰምተናል፡፡ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር የተፈለገው ነጥብ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም አይችልም ማለታቸው አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ፣ ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከተው አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በ26.10.96 ዓ.ም የተሰጠው ነው፡፡ ይህ ውሣኔ ሦስት አባላት ባሉት የሽምግልና ጉባዔ የተሰጠ ነው፡፡ የሽምግልና ጉባዔው ሊቋቋም የቻለው ጉዳዩ ስለህበረት ስራ ማህበራት በወጣው አዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት መታየት ያለበት በሽምግልና ነው ተብሎ በፍ/ቤት ቀደም ሲል በመበየኑ ምክንያት እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሠረት የሽምግልና ጉባዔው ከተቋቋመ በኋላም አመልካች በከሣሽነት፤ተጠሪ ደግሞ በተከሣሽነት ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በመጨረሻም ጉባዔው ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የሽምግልና ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሽምግልና ጉባዔውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አመልካች የአፈፃፀም ክሱን ያቀረበችው ከዚህ በኋላ ነው፡፡

እንደምንመለከተው በፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ብይን መሠረት ሦስት አባላት ያሉት የሽምግልና ጉባዔ ከመቋቋሙም በላይ፤ አመልካች እና ተጠሪም የጉባዔውን ስልጣን በመቀበል ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ውሣኔውን የሰጠው የሽምግልና ጉባዔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 215(1) እንደተመለከተው በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ ሊሰጥ የሚችል አካል ነው ማለት ነው፡፡ በግልግል ወይም በቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የተሰጠ ውሣኔ የሚፈፀመው በመደበኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሚፈፀምበት አይነትና ሁኔታ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 319(2) በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ግን ይህን በግልጽ የተመለከተውን ሕግ የተከተለ